# የኢፈርትና ሜድሮክ የቢዝነስ (ሞኖፖሊ) ኢምፓየር በኢትዮጵያ

ከሚሊዩን ዘ አማኑኤል

በጥላቸው የገዙ!

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በሁለት ትልልቅ የቢዝነስ ሞኖፖሊዎች ቁጥጥር ስር ይገኛል፡፡ አንደኛው በህወሃት የፖለቲካ ድርጅት የሃብት ቁጥጥር ስር የሚገኘው በስጦታ የተሳለፈ ሃብት ለትግራይ መልሶ ማቆቆም The Endowment Fund For The Rehabilitation of Tigrai (EFFORT) የሚባል ሲሆን የዚህም የሃብት ምንጭ ህወሃት በሽፍትነት ለአስራ ሰባት ዓመታት ከኢትዮጵያ ህዝብ የዘረፈው ሃብት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ (ሜድሮክ) ሞሃመድ ዓለም ዓቀፍ የእድገትና ጥናት ድርጅት ካንፓኒዎች Mohamed International Development Research Organization Companies (MIDROC)

የሚባለው በሳዑዲ ዓረቢያ ዜጋና ተወላጅ በሆነው ቢሊዩነር በሼክ መሃመድ አላ-አሙዲ ሃብት ነው፡፡ ሁለቱ ድርጅቶች በመጠቃቀም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚን ያለአንዳች ተቀናቃኝ በሞኖፖል በመቆጣጠር ለሃያ አመታት በላይ የሃገሪቶን ሃብት በዝብዘውታል፡፡

በመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ባለፈው 20 አመታት 365 መንግስታዊ ድርጅቶች ወደ ግል ዘርፍ ከተዘዋወሩት ውስጥ የኢፈርትና ሜድሮክ የቢዝነስ ሞኖፖሊዎች አብዛኛዎቹን በመግዛት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለመቆጣጠር ችለዋል፡፡ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የተሸጡትን ንብረቶች ወደግል ባለቤትነት እንዴት እንደሚያዘዋውር እንመልከት፡፡

1-ገዥው 35 በመቶ የመጀመሪያ ክፍያ ወይም ቃብድ (Down payment) በገንዘብ ይከፍላል፡፡((35% upfront-before signature of contract.)

2-ቀሪውን 65 በመቶ በአምስት ዓመታት ውስጥ ከፍሎ መጨረስ ይጠበቅበታል፡፡ (The remaining 65% shall be paid evenly within a maximum of five years.)ይህውም 65 ሲካፈል ለ5 ዓመት ይሆናል ስለዚህ በየአመቱ 13 መክፈል ይጠበቅበታል፡፡

ለምሳሌ አዲስ አበባ መስቀል አደባባይ ከእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ፍት ለፊት የነበረው ራንዴቩ ካፍቴሪያ ወይም አብዩት ራንዴቩ በመባል የሚታወቀው በወ/ሮ እንይሽ አስረስ የሼክ መሃመድ አላ-ሙዲ ሚስት በ2,800,000 ሚሊዩን ብር ሲገዙት ገዥው 35 በመቶ የመጀመሪያ ክፍያ ወይም ቃብድ (Down payment) 980,000 ሺህ ብር በገንዘብ ትከፍላለች፡፡ ቀሪውን 1,820,000 ሚሊዩን ብር ሲሆን በየአመቱ 364,000 ብር መክፈል ይኖርባታል ማለት ነው፡፡

3- በቀሪውን 1,820,000 ሚሊዩን ብር ላይ በየአመቱ የባንክ ወለድ ይታሰባል (the prevailing average bank's deposit interest rate shall be applied on the unpaid balance.

ሌላ ምሳሌ ለመጥቀስ የአዋሳ ዱቄት ፋብሪካ ለአበባ ግደይ ኃ/የ/የግ ድርጅት (የኢፈርት ድርጅት) በሚል ሽፋን በ18,509,250.00 ሚሊዩን ብር ሲሸጥ አበባ ግደይ የመሸጫ ዋጋውን 35 በመቶ 6,478,237.5 ሚሊየን ብር የመጀመሪያ ክፍያ ወይም ቃብድ (Down payment) በመክፈል ቀሪውን 12,031,012.5 ሚሊየን ብር በአምስት አመታት ውስጥ 2,406,202.5 ሚሊየን ብር በየአመቱ

በመክፈል እዳቸውን መዝጋት ይጠበቅባቸዋል። በጣም የሚገርመው አበባ ግደይ የአዋሳን ዱቄት ፋብሪካ ገዝተው የፍብሪካውን የባንክ ተቀማጭ ጥሬ ገንዘብ 20 ሚሊዬን ብር ወደ ግል ሃብታቸው ማዘዋወራቸው ሠራተኛው ሁሉ የሚያውቀው፤ የደቡብ ክልል መንግስት የሚያውቀው፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚያውቀው አለም ያወቀው ፀሃይ የሞቀው የህወሃት/ኢህአዲግ መንግስት ከአጥንታቸው መቅኒ የደረስና የዘለቀ የሙስና ባህል የነድር ቤቱ የሽፍቶች መንግስት ፋብሪካውን የሸጡበት ቀን 7/3/2000 አ.ም በፊት የኢትዮጵያ ህዝብ ንብረትን ለመዝረፍ አልመው የመጡ መሠረተ ደሃ የህወሃት/ኢህአዲግ ካድሬዎች ዋነኛ ዓላማ ነበር። እንዲህ ያለ አስገራሚ የሙስና ታሪኮች ብዙ ጥራዝ የሚወጣቸው መፃህፍት እንደሚወጣቸው ይታመናል። የአበባ ግደይ ድርጅት ፋብሪካውን በማስያዝ ከባንክ ምን ያህል ሚሊዬን ብር እንደተበደረበት ለግዜው አይታወቅም። ሁሉም ባለሃብቶች ከባንክ የገዙትን ድርጅት በማስያዝ በብዙ ሚሊዬን ብር ስለሚበደሩበት (የፋብሪካው እዳና የባንክ ብድር) ታክሎበት ባለሃብቱን ንብረት የሚገዛ ስለማይገኝ መንግስትና ኤጀንሲው እዳውን ያልከፈለ ባለሃብትን ምንም ማድረግ ስለማይችል ዝም ማለትን ይመርጣሉ።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ወደ ግለሰብ ንብረትነት ለማዘዋወር በተደረገው የሃብት ሽግግር ለባለ ሃብቶቹ የመግዣ ገንዘብ በማበደርና ከገዙም በኃላ ለባለሃብቶቹ ገንዘብ በማበደር ትልቅ ሚናና ሙስና ተጫውቶል። እነዚህ በሁለት ትልልቅ የቢዝነስ ሞኖፖሊዎች ኢፈርትና ሜድሮክ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በሁሉም መስክ በግብርና፤በኢንደስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች ጠርንፈው በመያዝ በሃገሪቱ የግል ባለሃብቶችን እድገት ያጨነገፉ ህቡዕ የኢኮኖሚ የገነቡ የማፍያ ቡድን ናቸው።

ኢፈርት በ1997 እኤአ ‹ወጋጋን ባንክ› በማቀቀም በአሁኑ ግዜ ዘጠና ቅርንጫፍ ሲኖረዉ በ2011/12 እኤአ 458 ሚሊየን ብር ትርፍ ያገኘ ባንክ ቢሆንም ቅሉ፣የኢፈርት ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሶስት ቢሊዬን ብር ተበድረው ያልመለሱ የማፍያ ድርጅት ናቸው።

ሜድሮክ በ2003 እኤአ ‹ዳሽን ባንክ› በማቀቀም በአሁኑ ግዜ መቶ ሃያ ስድስት ቅርንጫፍ ሲኖረዉ በ2011/12 እኤአ 896 ሚሊየን ብር ትርፍ ያገኘ ባንክ ሲሆን ጠቅላላ ንብረቱ 20 ቢሊዩን ብር ይገመታል። የሜድሮክ ካንፓኒዎች ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሁለት ቢሊዬን ብር ተበድረው ያልመለሱ የማፍያ ድርጅት ናቸው። ሌላው ኒያላ ኢንሹራንስ ካንፓኒ ሌላው የሜድሮክ ንብረት ሲሆን በ1995 እኤአ ተመስርቶ በመላ ሃገሪቱ 30 ቅርንጫፎች ሲኖሩት ጠቅላላ ንብረቱ 166,800,000 ሚሊዬን ብር መሆኑ ይታወቃል።

| No | Bank Name | Owner | Year Est. | No of Branches | Profit in EB (2011/2012) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Wegagaen Bank | (EFFORT) | 1997 | 90 | 458,000,000.30 |
| 2 | Dashen Bank | (MIDROC) | 2003 | 126 | 896,000,000.50 |
| 3 | Nyala Insurance Company | (MIDROC) | 1995 | 30 | 166,800,000 Asset Value |

"When all former private insurance companies in Ethiopia were nationalized by the socialist regime that prevailed from 1974 to 1993, they were taken over by the government-owned insurance corporation. Following the change to a market-led economy in 1994, many private business institutions, including banks and insurance companies, were established. Nyala was the seventh to be licensed in July 1995. Nyala Insurance S.C., or NISCO, was established with 7 million Ethiopian birr in paid-up capital and 25 million birr in authorized capital. Nyala has raised its capital to 35 million birr in paid-up capital and 50 million birr in authorized capital, with an asset value of more than 166,800,000 birr. Nyala operates from more than 30 service centers located in all regions throughout the country." Source:-**www.nyalainsurance.com.**

መንግስት ወደ ግል ዘርፍ እንዲዘዋወሩ የወሰናቸውን ድርጅቶችና ፋብሪካዎች ወዘተ እሚገኙበትን የምጣኔ ሃብት፣የቴክኒክና የገንዘብና የመሸጫ ዋጋ ተመን በጥልቅ ጥናት ላይ በመመስረት ለጨረታ ማቅረብ፣ድርጅቶቹን ያሉበትን ሁኔታ፤ ዝርዝር የሰው ሃይል መረጃዎችን፣ ንብረቶችን፣ መዋዕለ

ንዋይና የህግ ሁኔታ ከመሸጣቸው በፊት በጥልቀት የማጥናት ሃላፊነት እንዳለባቸው ቢታወቅም ብዙዎቹ አትራፊ የነበሩ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የነበራቸውን ተቀማጭ ከአምስት እስከ ሃያ ሚሊዩን ብር የሚደርስ ተቀማጭ ገንዘብ ባለሃብቱ ድርጅቱን በገዛ ማግስት ገንዘቡን ወደ ግል አከውንቱ በማዘዋወር በነፃ የተረከብ ባለሃብቶች እንደነበሩ ማስረጃዎቹ በጥናት ያረጋግጣሉ፡፡

ጉቦ ሰጭም፤ ተቀባይም፤ አገናኝም ወንጀለኞች ናቸው፡፡ በኤጀንሲው ውስጥ የሚገኙ ሠራተኞች በግዜዊ ጥቅም ተደልለው የሃገር ሃብት ሲዘረፍ ለወደቀላቸው ትራፊ ቢረቱም ከዚህ ስራቸው ለመንፃት የሚያውቁትን በመፃፍ ለህዝብ ማሳወቅና ወደ ግል ዘርፍ የተላለፉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች፣ ፋብሪካዎችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችን እንዴት የኢፈርትና ሜድሮክ የቢዝነስ ሞኖፖሊዎች እና ሌሎች ባለሃብቶች ንብረትነት እንደተዘዋወሩ መረጃዎቹን በማሰባሰብ ለህዝብ ማሳወቅ ይህን ግልፅነት በጎደለው ሁኔታ ወደ ግሉ ዘርፍ መተላለፋቸውን መመስከር የግዜው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡ ቀጥሎ የህወሃት/ኢህአዲግና የኢፈርት የገዙትን ድርጅቶች ለናሙና ያህል እንጠቅሳለን፡፡

ቀጥሎ (ሜድሮክ) ሞሃመድ ዓለም ዓቀፍ የእድገትና ጥናት ድርጅት ካንፓኒዎች Mohamed International Development Research Organization Companies (MIDROC) የሚባለው በሳዑዲ ዓረቢያ ዜጋና ተወላጅ በሆነው ቢሊዩነር በሼክ መሃመድ አላ-አሙዲ ከመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ያለተቀናቃኝ (ያለተወዳዳሪ) በሞኖፖሊ ወደ ግልሃብታቸው ያዘዋወሩት የኢትጵያ ህዝብ ንብረቶች በዝርዝር ለናሙና ያህል ይቀርባል፡፡ አንዱና ሁለት ድርጅቶች በሞኖፖሊ የሃገሪቱን ኢኮኖሚና ሃብት ከተቆጣጠሩት ግልጽነት የሌለው አሰራር፤ ሙሰኝነት፤ አድሎ ፤ፈላጭ ቆጭነት፤ ወዘተ ይሰፍናል፡፡ የሃገሪቱን ኢኮኖሚ ብዙ ባለሃብቶች ከተቆጣጠሩት የሃብት ክፍፍሉ የተመቻቸ ይሆናል፡፡

## <u>ሜድሮክ የወርቅ ማዕድን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር</u>

<u>(MIDROC Gold Mine Pvt Ltd. Co. (MGOLD)</u>

ህወሃት/ኢህአዲግ ለሼክ መሃመድ የወርቅ ማዕድን የሸጠላቸውን መለስ ዜናዊና የእሳቸው የረከሰ ግንኙነት መጋለጡ ስለማይቀር የነብርን ጭራ ከያዙ አይለቁ ሆኖባቸው ነው፡፡ ለዚህም ነው ኢንቨስተሩ የደደቢት ህወሃት የጦር አበጋዞች፣ የፖለቲካ ካድሬዎችና የብአዴን፣ የኦህዴድ፣ደህዴድ ወዘተ ባለስላጣኖች በታመሙ ቁጥር ውጭ ሃገር በማሳከም ስርዓቱን በታማኝነት ሲያገለግሉ የሚስተዋሉት፡፡ እንደ አህዬች ‹እከክልኝ ልከክልህ› ሚጥሬን ደብቅልኝ ልደብቅልህ ነው ጨዋታዉ፡፡ አንድ ቀን ሚስጥሩ ሁሉ ይወጣል፡፡

ሜድሮክ የወርቅ ማዕድን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር (MIDROC Gold Mine Pvt Ltd. Co. (MGOLD) የሜድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ አካል ነው፡፡ የሜድሮክ የወርቅ ማዕድን በ1990 እኤአ በሼክ መሃመድ ሁሴን አላ-አሙዲና በሚስታቸው ሶፊያ ሳላህ አላ-አሙዲና በኢትዮጵያ መንግስት 51.6 ሚሊዬን ዩኤስ ዶለር መነሻ ካፒታል የተቆቆመ ድርጅት ነው፡፡ ከብሄራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ( National Mining Corporation (NMC) ከተቆቆመ ጥቂት አመታት በኃላ ሜድሮክ የወርቅ ማዕድን ተመሰረተ፡፡ በ1997 እኤአ የህወሃት/ኢህአዲግ መንግስት ለሜድሮክ የወርቅ ማዕድን (የወርቁ ክምችት መጠኑ 37,215 ኪሎግራም ነበር) በ172 ሚሊዬን ዩኤስ ዶለር የለገደንቢን የወርቅ ማዕድን ለሃያ አመታት ፈቃድ ሸጡት፡፡ ሌላው በእምራብ ሳካሮ በ 33.57 እስኩየር ኪሎሜትር ራዲየስ /ኩታገጠም ቦታ ውስጥ እስከ ለገደንቢ የሚገኝ ሲሆን የወርቁ ክምችት 17,250 ኪሎግራም ነው፡፡

| No | Place | Region | Gold reserve Kg | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | MIDROC Gold Mine Pvt Ltd. Co. (MGOLD | | | 51.6 |
| 2 | Legadembi | | 37,215 | 172 |
| 3 | Metekel Zone (Jila) | Benshangul | 33,000 | |
| 4 | East Sakaro | | 17,250 | |

የለገደንቢን የወርቅ ማዕድን  በደቡብ አዲስ አበባ 500 ኪሎ ሜትር  ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ የሜድሮክ የወርቅ ማዕድን በአዶላ- ለገደንቢ የማዕድን አሰሳ ፍቃድ ሲኖረው አጠቃላይ አመታዊ ምርት 1.6 ሚሊዬን ቶን ያልነጠረ የብረታብረት አፈር ያመርታል፡፡ አመታዊ አማካኝ ምርት 4,500 ኪሎ ግራም የወርቅና ፣ብር ቅልቅል ተመርቶ በመጨረሻው 3,500 ኪሎ ግራም  የነጠረ የወርቅ ምርት ያመረታል፡፡ ለወርቅ ማዕድን 78 በመቶ አማካኝ ተገቢ ጥራት፤ለብር ማዕድን 21 በመቶ  አማካኝ ተገቢ ጥራት፤ ቀሪው 1 በመቶ ሌላ ማዕድናት ሲሆኑ ምንም የግብይይት ዋጋ የላቸውም፡፡ ከዚያም የወርቅ ማዕድን ባር/ጥፍጥፍ ወደ ሲዊዘርላንድ ሃገር ‹‹አርጎር ሄራውስ›› ማጣሪያ ይላካል፡፡ ቀጥሎም የወርቅ ማዕድን ተጣርቶ የመጨረሻው የወርቅ ባር ምርቱ ዙሪክ ሲዊዘርላንድ በሚገኘው የንግድ ባንክ ይሸጣል፡፡ በጣም የሚገርመው የሽርክና ስምምነት ታዲያ፤ የሜድሮክ የወርቅ ማዕድን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር ባለቤት ሼክ መሃመድ ሁሴን አላ-አሙዲ የባለቤትነት ድርሻ 98 በመቶ ሲሆን የህወሃት/ኢህአዲግ  መንግስት ድረሻ 2 በመቶ በንግድ ሽርክና ላይ የተመሠረተ ካንፓኒ መሆኑ ነው፡፡ የኢትዬጵያ ህዝብ ህወሃት/ኢህአዲግ በክልሎች ከፋፍሎት የአንዱ ክልል ህዝብ ሌላውን ህዝብ ከክልሌ ውጣ ከሚባባል ይሄን የወርቅ ማዕድን በማስመለስ ለኢትዬጵያ ህዝብ ጥቅም የሚውልበትን መንገድ መፈለግ የተሻለ አማራጭ ነው፡፡ ለሼክ መሃመድ የወርቅ ማዕድን ሰጥቶ አንዱን ደሃ ገበሬ ክልሌን ለቀህ ውጣ አትውጣ ማለት ‹‹አህያውን ፈርቶ ዳውላውን!›› ወይም ድመት እንዳለችው ‹‹ ምን ቢታለብ በገሌ!›› አይሆንምን፡፡ እኛ በብሄር ብሔረሰብ፤በሃይማኖት ወዘተ፤  አንዱ ከአንዱ ሲጣላ ወርቁ ተዝቆ ያልቃል፡፡ ልብ ያለው ልብ ይበል!!!

በ2009 እኤአ ኢትጵያ ብሔራዊ ባንክ በአለፉት አስር አመታት ውስጥ 48 ቶን (480 ኪሎ ግራም) ወርቅ ኤክስፖርት/ወደ ውጭ ሃገር በመላክ  540.5 ሚሊዬን ዩኤስ ዶለር ገቢ አግኝቶል፡፡ ከዚሁ ውስጥ 47.9 ቶን (470.9 ኪሎ ግራም) ወርቅ ምርት ከሜድሮክ ለገደንቢ የወርቅ ማዕድን የተገኘ ሲሆን ፤ቀሪው ከባህላዊ የወርቅ ማዕድን አምራቶች 693.3  ኪሎ ግራም የወርቅ ምርት 20 ሚሊዬን ዩኤስ ዶለር እንደተገኘ ተገልፆል፡፡

## Financial Information

In October 2009 the National Bank of Ethiopia said that Ethiopia earned US$ 540.5 million from nearly 48 tonnes of gold exports in the last 10 years. Approximately 47.9 tonnes, worth US$520.5 million, was produced by the Lege Dembi mine, run by Midroc.

The balance of 693.3 kg worth US$20 million was produced by artisanal miners.

ምንጭ፡ ሜድሮክ ድረ-ገፅ

ሜድሮክ በሌላ ቦታ ደግሞ በሰሜን ምስራቅ አዲስ አበባ 600 ኪሎ ሜትር ርቀት በመተከል የማዕድን አሰሳ ፍቃድ አለው፡፡የሜድሮክ የወርቅ ማዕድን ሃላፊነቱ፤ የግል ድርጅት 7, 2011 ሰብ ሰሃራ መረጃ በወጣው ዜና መሰረት 33,000 ኪሎግራም ያለው የወርቅ የማዕድን ክምችት በቤኒ ሻንጉል ጉምዝ  ክልላዊ መንግስት  ማግኘቱ ተገልፆል፡፡ በዛን ግዜ ባለው የዓለም ዓቀፍ ንግድ የወርቅ ገበያ መሠረት የተገኘው ወርቅ ዋጋው ሲሰላ 19 ቢሊዬን ብር እንደሚሆን ተገምቶል፡፡  የወርቅ ማዕድን ክምችቱ በኢዬጵያውያን ኤክስፐርቶች ምርምር የተገኘ ሲሆን ቦታውም (በቀድሞው ጎጃም ክ/ሃ) በመተከል ዞን ጂላ በሚባል ቦታ በአሁኑ የኢህአዲግ አከላለል ቤኒ ሻንጉል ጉምዝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ካንፓኒው የወርቅ ማዕድን ማሽን ተክሎ የወርቅ ምርቱን ማውጣት ጀምሮል፡፡ ካንፓኒው ከመንግስት 7,000 ሄክታር መሬት በመውስድና 46 ሚሊየን ብር መዋለ-ንዋይ/ኢንቨስት/ በማድረግ የወርቅ ማዕድን ምርት በማምረት ላይ ይገኛል፡፡ በ1998 እኤአ ካንፓኒው ከማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ፍቃድ ተሰጥቶት ሥራውን ጀምሮል፡፡ይህ አዲሱ ቦታ  በሜድሮክ ካንፓኒ ሶስተኛው ትልቁ የወርቅ ማዕድን ክምችት ያለበት ስፍራ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

የህወሃት/ኢህአዲግ  መንግስት የወርቅ ማዕድን የሚያህል የህዝብ ሃብት ለውጭ ሃገር ባለሃብት ሰጥቶ፤ የአንበሳ አውቶብስ፣ የቴሌ ኮምኒኬሽን፣የቡናና የጫት ንግድ የመሳሰሉትን በመንግስት ንብረትነት ይዞ መንገታገቱ ምን የሚሉት የኢኮኖሚክስ ጥናት ይሆን!!! የመለስ ዜናዊ ልማታዊ መንግስት ለግለሰብ የወርቅ ማዕድን ሰጥቶ የህዳሴ ግድብ ተሰርቶ ፤ኤሌትሪክ ለጎረቤት ሸጦ፤ ዶለር አምጥቶ፣ የኢትዬጵያን ህዝብ ወደ መካከለኛ ገቢ ሃገር አሸጋግራታለሁ የሚለው ዲስኩር ‹‹ላም አለኝ በሰማይ ወተቶንም አላይ!!!›› አይሆንምን!!! ይልቅ የህወሃት/ኢህአዲግ ነፃ ያልወጡ ነፃ አውጭዎች ከኢፈርትና ሜድሮክ የቢዝነስ ኢምፓየርና ሞኖፖሊ ነፃ ቢያወጡት ይመረጣል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም፤የክልል መንግስታቶችና የፓርላማ ተመራጮች ይሄን የህዝብ ጥያቄ ማድረግ አለባቸው፡፡ ከሼክ መሃመድ ሁሴን አላ-አሙዲ ከ300ኛ የዓለም ሃብታሞች ወደ 100ኛና ከአፍሪካ አንደኛ የሆነበት ሚስጥር ይሄን የወርቅ ማዕድን ከዛቀበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡ ከሼክ መሃመድ ሁሴን አላ-አሙዲ የነጋዴዎች ተምሳሌት (Role Model) ያልሆነ ቦዘኔ ነጋዴ ነው፡፡ ለእሱ ሲሆን ከ10 እስከ 15 አመታት ሳይሰራበት አጥሮ ያስቀመጠው እልፍ ቦታ (በፒያሳ መንትዬቹ ፎቆች፤ አብዮት ራንዴቩ፤ ሆራ ራስ ሆቴል፤ሻሸመኔ- አዋሳ እርሻ፤ ናኒ ህንፃ ወዘተ) በየቦታው ያለ፤ የኢትዬጵያ ህዝብ ይቁጠረው!!! ማን ሊነካቸው!!! ሲሶ መንግስት ማለት ከዚህ በላይ ምን አለ!!!፣ህጉ፤ ህገመንግስቱ በሼክ አላ-አሙዲ የጥንቆላ ጥበብ እንደ አሊባባ(ሼክ)ና አርባዎቹ ሌቦች(ኢፈርት) የዋሻው የመክፈቻውና የመዝጊያው ህቡዕ ኮድ ሼኩ ስላላቸው የህወሃት/ኢህአዲግ ሆዳም ሹማምንትን ተከፈቱ ተዘጉላቸው፡፡

MIDROC Ethiopia Construction Plc. is established in 1993, with a total investment in construction equipment plant and facilities of Birr 500 million and engaged in a wide range of construction undertakings of all types and sizes. MIDROC Ethiopia Construction Plc.the Company has undertaken several multi million birr projects in Ethiopia. To mention a few:

| No | Description | Owner | *Total investment* (in Birr) | *E*stablished Date |
|---|---|---|---|---|
| 1 | *MIDROC Ethiopia Construction Plc.* | *MIDROC* | 500,000,000 | 1993 |
| 2 | *Sheraton Addis Hotel* | *MIDROC* | | |
| 3 | *Nani MIDROC Corporate Office Building* | *MIDROC* | | |
| 4 | *Mekele Referral Hospital Building* | Tigray State | | |
| 5 | *Pharmacure pharmaceuticals manufacturing factory* | PPMF | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 6 | *African Union Conference Hall & Office Complex* | *African Union* | | |
| 7 | *Oromia State Conference Hall & Office Complex* | *Oromia State* | | |
| 8 | *Loli Office and Residential Building* | *Loli* | | |
| 9 | *Amhara Martyr's Monument* | *Amhara State* | | |
| 10 | *Federal Police Head Quarters* | *Federal Police* | | |
| 11 | *Ethiopian Airlines Cargo Terminal* | *Ethiopian Airlines* | | |
| No | Description | Owner | *Total investment* (in Birr) | *Established* Date |
| **MIDROC Ethiopia Group Companies :- Owned by Sheikh Mohammed Hussein Ali Al-Amoudi** | | | | |
| 1 | ADDIS INTERNATIONAL CATERING PLC | Al-Amoudi | | |
| 2 | ETHIO AGRI-CEFT PLC | Al-Amoudi | | |
| 3 | ETHIO LEATHER INDUSTRY PLC (ELICO) | Al-Amoudi | | |
| 4 | KEBIRE ENTERPRISE PLC | Al-Amoudi | | |
| 5 | LAME DAIRY PLC | Al-Amoudi | | |
| 6 | MAMCO PAPER PRODUCTS PLC | Al-Amoudi | | |
| 7 | MIDROC CONSTRUCTION ETHIOPIA PLC | Al-Amoudi | | |
| 8 | MIDROC ENERGY HOUSE ELECTRO-MECHANICAL SERVICES PLC | Al-Amoudi | | |
| 9 | MIDROC FOUNDATION SPECIALIST PLC | Al-Amoudi | | |
| 10 | MOHA SOFT DRINKS INDUSTRY SC | Al-Amoudi | | |
| 11 | MUGAD TRAVEL PLC | Al-Amoudi | | |
| 12 | NATIONAL MINING CORPORATION PLC | Al-Amoudi | | |
| 13 | NATIONAL OIL ETHIOPIA PLC (NOC) | Al-Amoudi | | |
| 14 | PHARMACURE PLC | Al-Amoudi | | |
| 15 | SALAM HEALTH CARE PLC | Al-Amoudi | | |
| 16 | SHERATON ADDIS | Al-Amoudi | | |
| 17 | STAR SOAP AND DETERGENT INDUSTRIES PLC | Al-Amoudi | | |
| 18 | UNLIMITED PACKAGING PLC | Al-Amoudi | | |

| No | Description | Owner | *Total investment* (in Birr) | *Established* Date |
|---|---|---|---|---|
| **MIDROC Ethiopia Affiliate Companies :- Owned by the close relatives(family) of the Chairman.** | | | | |
| 1 | CABEY PLC | Al-Amoudi family | | |
| 2 | EAST WEST ETHIO TRANSPORT PLC | Al-Amoudi family | | |
| 3 | EQUATORIAL BUSINESS GROUP PLC | Al-Amoudi family | | |
| 4 | NATIONAL MOTORS CORPORATION PLC | Al-Amoudi family | | |
| **MIDROC Ethiopia Projects Under Implementation** | | | | |
| 1 | AWASSA CHIPWOOD PLANT PROJECT | | | |
| 2 | DERBA 5000 TPD CEMENT PLANT PROJECT | | | |
| 3 | HORA FOOD COMPLEX PROJECT | | | |
| 4 | HOTEL PROJECTS | | | |
| 5 | METI (MIDROC EDUCATION AND TRAINING INSTITUTE) | | | |

Source:-For MIDROC Ethiopia Technology Group companies visit the website: www.midroc-ethiotechgroup.com

## The Endowment Fund For The Rehabilitation of Tigrai (EFFORT)

**በህወሃት የፖለቲካ ድርጅት የሃብት ቁጥጥር ስር የሚገኘው ለትግራይ መልሶ ማቋቋም በስጦታ የተላለፈ ሃብት** The Endowment Fund For The Rehabilitation of Tigrai (EFFORT) **የሚባል ሲሆን የዚህም የሃብት ምንጭ ህወሃት በሽፍትነት ለአስራ ሰባት ዓመታት ከኢትዮጵያ ህዝብ የዘረፈው ሃብት ነው። ኢፈርት ምንም እንኮን በትግራይ ሕዝብ ስም እያጭበረበረ፤ ጥቂት የደደቢት ህወሃት ካድሬዎችና የጦር አበጋዞች ንብረትነት ንግዱን በሞኖፖል በመቆጣጠር የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚበዘብዙበት ‹የማፍያ› ሕቡዕ የንግድ ተቋም ነው። ከዚህ ቀጥሎ የህወሃት ካንፓኒዎች በኢፈርት ስር ያሉትን፤ የተመሰረቱበት አመተ-ምህረት፣የካፒታላቸው መጠን፤ዋና ፅህፈት ቤታቸውና የሚያስተዳድሩት የቦርድ ሊቀመንበር በዝርዝር ይቀርባል።**

- **Full List of TPLF Companies Under EFFORT**
- **<u>Companies with investment capital of < 20,000,000 Million Ethiopian Birr</u>**

**Companies with investment capital of < 20,000,000 Million Ethiopian Birr**

| Company Name | Year Est.(EC) | Capital | HQ | Board Chairman |
|---|---|---|---|---|
| Selam Transport | 1995 | 10,000000 Birr | Mekele | Arkebe Ekubay |
| Segel Construction | 1995 | 10,000,000 Birr | Mekele | Araya Zerihun |
| Mega Net Corp | 1995 | 10,000,000 Birr | Mekele | Alemseged Gebreamlak |
| Hitech Park Axion Association | 1995 | 10,000,000 Birr | Mekele | Shimelis Kinde |
| Fana Democracy plc | 1995 | 6,000,000 Birr | Mekele | Negash Sahle |
| Express Transit | 1995 | 10,000,000 Birr | Mekele | G/selassie Gidey |
| Ethio Rental Axion Association | 1995 | 10,000,000 Birr | Mekele | Atkilit Kiros |
| Dilate Brewery | 1995 | 15,000,000 Birr | Mekele | Kahsay TewoldeTedla |
| Dessalegn Caterinary | 1995 | 15,000,000 Birr | Mekele | Dr, Maru Erdaw |
| Addis Consultancy House | 1995 | 10,000,000 Birr | Mekele | Sibhat Nega |
| Birhane Building Construction | 1995 | 10,000,000 Birr | Mekele | Bereket Mazengiya |
| **Total Capital** | | **116, 000,000 birr** | | |

**<u>Companies with investment capital between 20-49 Million Ethiopian Birr</u>**

| Company Name | Year Est (EC) | Capital | HQ | Board Chairman |
|---|---|---|---|---|
| Sheba Tannery Factory Axion Assoc. | 1995 | 40,000,000 Birr | Wukro | Abadi Zemu |
| Meskerem Investment | 1995 | 40,000,000 Birr | Axum | Tewodros Ayes Tesfaye |
| Africa Insurance Axion Association | 1995 | 30,000,000 Birr | A.Ababa | Yohannes Ekubay |
| Global Auto Sparepart | 1995 | 26,000,000 Birr | A.Ababa | Teklebirhan Habtu |
| Experience Ethiopia Travel | 1995 | 26,000,000 Birr | Mekele | Tony Hiki |
| Addis Engineering Consultancy | 1995 | 25,000,000 Birr | A.Ababa | Arkebe Ekubay |
| Hiwot Agriculture Mechanization | 1995 | 25,000,000 Birr | Mekele | Yohannes Kidane |
| Berhe Chemical Axion | 1995 | 25,000,000 Birr | Mekele | Abadi Zemu |
| Rahwa Yebegina Fiyel Export | 1995 | 25,000,000 Birr | Mekele | Yassin Abdurahman |
| Star Pharmaceuticals | 1995 | 25,000,000 Birr | Mekele | Arkebe Ekubay |
| Tesfa Livestock | 1995 | 20,000,000 Birr | Mekele | Yohannes Kidane |
| **Total Capital** | | **307,000,000 Birr** | | |

**Companies with a paid-up capital of >50.000.000  Million Ethiopian Birr**

| Company Name | Year Est.(EC) | Capital | HQ | Board Chairman |
|---|---|---|---|---|
| Almedan Garment Factory | 1995 | 660,000,000 Birr | Mekele | Abadi Zemu |
| Mesfin Industrial Company | 1995 | 500,000,000 Birr | Mekele | Arkebe Ekubay |
| Mesob Cement Factory | 1995 | 240,000,000 Birr | Mekele | Abadi Zemu |
| Almeda Textile Factory | 1995 | 180,000,000 Birr | Mekele | Abadi Zemu |
| Sur Construction | 1995 | 150,000,000 Birr | A.Ababa | Arkebe Ekubay |
| Trans Ethiopia | 1995 | 100,000,000 Birr | Mekele | Shimelis Kinde |
| Dedebit Saving & Loan | 1995 | 60,000,000 Birr | Mekele | Atkilit Kiros |
| Ezana Mining Development | 1995 | 55,000,000 Birr | A.Ababa | Tewodros H. Berhe |
| Addis Pharmaceuticals Production | 1995 | 53,000,000 Birr | A.Ababa | Abadi Zemu |
| Tana Trading House Axion Association | 1995 | 50,000,000 Birr | A.Ababa | Sibhat Nega |
| **Total Capital** | | **1,868,000,000 Birr** | | |

**Companies that did not make their paid-up capital public**

| | | | |
|---|---|---|---|
| Ambassel Commerce | Dinsho Share Company | Tigrai Tagai Association | Brook Chemical Share Company |
| Dashen Beer Factory | Express Ethio Travel Service | Tigrai Development PLC | Computer Networking Technology |
| Amhara Meleso MaquaQuam | Berhan Building Construction | Star Pharmaceutical Importers | National Electromechanical |
| Saba Emnebered | Guna Trade Services | Biftu Dinsho | Oromia Credit Bank |
| Adwa Flour Factory | Wendo Trading | Shala Advertisement | National Geo-Textile |
| Trans Ethiopia | Tikal Agri Tigrai | Wegagen Bank | Alage Forest Products |
| Sebhat Nega PLC | Addis Transport | Walta Industry | Martha poultry |
| Dima Honey Processinf plant | Zeleke Agricultural Mechanization PLC | Tikur Abbay Transport | Beruk Tesfa Plastic Factory |
| Aberdele Animal Export Company | Maichew Particle Board | | |

These 66 companies are owned and managed by ethnic Tigreans
**Some Board Chairmen might have moved within the parastatals*
**The amount shown on the tables above are initial start up capitals. The total networth of the parastatals has quadrupled.*

## <u>የኢፈርትና ሜድሮክ የከተማ ቤቶች ቅርምት</u>

በ1967 ዓም የኢትዮጵያ ወታደራዊ መንግስት (ደርግ) በሃገሪቱ ውስጥ የሚገኙ በግል ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን በአዋጅ ቁጥር 20/1974 ወደ መንግስት ሃብትነት በማዘዋወርና በመውረስ ፋብሪካዎች፣ባንኮችና ኢንሹራንሰ ኩባንያዎችን፣የከተማ ትርፍ ቤቶችን፣ የገጠር መሬትን፣ እርሻዎችን ወዘተ በብሄራዊ ሃብትና እድገት ሚኒስትር( Ministry of National Resource Development) ስር የተወረሱትን ንብረቶች እንዲያስተዳድር ስልጣንና ሃላፊነት በአዋጅ ተሰጠው።

በዚህም መሠረት፣የከተማ ትርፍ ቤቶችን አዋጅ ለማስፈፀም የመንግስት ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ተቆቁሞ የወር ኪራያቸው ከመቶ ብር በታች የሆኑትን ቤቶች በቀበሌ አስተዳደር ስር እንዲተዳደሩ ተወሰነ። የወር ኪራያቸው ከመቶ ብር በላይ የሆኑትን ቤቶች በመንግስት ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እንዲተዳደሩ ተወሰነ። የደርግ ወታደራዊ ሹማምንቶችና ቢሮክራቶች፤የኢሠፓ፤መኢሶን፤ወዝሊግ፤ ኢጭአት፤ማልሪድ፤ሰደድ ካድሬዎች የተወረሱትን ቤቶቹን በነፃ ኪራይ ተቀራመቶቸው። ከ1967 እስከ 1983 አ.ም ድረስም ቤቶቹን ለግል ጥቅማቸው ተጠቀሙባቸው። ብዙ ሸህ ህፃናት የጎዳና ተዳዳሪዎች በሚኖሩባት ሃገር እነዚህ ሰቀቀናም የነቀዙ የጦር አበጋዞችና የፖለቲካ ካድሬዎች አገሪቶን አቆረቆዙ።ወታደራዊው መንግስት፤የገጠር መሬትንና የከተማ ትርፍ ቤቶችን በአዋጅ

ቢወርስም ቅሉ መሬት በመሸጥ፣ሊዝና ኮንትራት በማድረግ ተግባር ላይ አልተሰማራም። የመንግስት ገቢ ከህዝብ ከሚሰበስበው ግብር(ታክስ) እንጂ መሬት በመሸጥ ላይ አልነበረም።
የህወሃት/ኢህአዲግ መንግስት፤ የከተማ መሬት በመሸጥ፤የገጠር መሬት በሊዝና ኮንትራት ከ 60 እስከ 90 አመታት ለውጭ ሃገር ባለሃብቶች በመሸጥ የኢትዮጵያን ህዝብ የመንግስት ጭሰኛ ያደረገ በእውቀት የጨነገፈ የደደቢት ደደቦች መንግስት ነው። የኢትዮጵያን ህዝብ የግል ንብረት የማፍራት መብቱን ተነጥቆ በመሬቱ ላይ የመጠቀም መብት ብቻ እንዳለው በህወሃት/ኢህአዲግ መንግስት ህገመንግስት ተደንግጓል። ከ1983 አ.ም የህወሃት/ኢህአዲግ መንግስት፤ በከተማ ልማት፤ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፤የመንግስት ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ(የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ) በመቆጣጠር በአዲስ አበባና በሌሎች አገሪቱ ክልሎች የሚገኙ በድምሩ 17,549 ቤቶች ማስተዳደር ጀመረ። ከዚህ ውስጥ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ አስተዳደሮች በድምሩ 1,242 መኖሪያ ቤቶችና 5,507 የድርጅት ቤቶች መኖራቸውን የግል ኩባንያው በጥናቱ መረጃ ያረጋግጣል።

- According to the Planning Commissioner, Office for the Revision of Addis Ababa Master Plan (ORAAMP), housing is a "high priority" for the City, for several reasons: Of the roughly 150,000 *kebele* housing units in Addis today, 70-80 percent will cease to exist in 20 years' time due to their poor quality of construction.
- Government Housing:-This comprises housing for government employees and constitutes about 34 percent of the formal housing stock, which includes roughly 16,000(17,549 based on the new study) rental housing units managed by the Rental Housing Authority (RHA).17 These are mostly units acquired by the government during nationalization, which had rents above 100 Birr per month.

የህወሃት/ኢህአዲግ መንግስት ከ1983 አ.ም ጀምሮ እስከአሁን እነዚህን መኖሪያ ቤቶች ለህወሃት፣ብአዴን፣ኦህዴድ፣ወዘተ የጦር አበጋዞችና የፖለቲካ ካድሬዎች ከደርግ ሹማምንትና ካድሬዎችን ከቤታቸው እያስወጡ በነፃ ተቀራመቶቸው። የሚገርመው እነዚህ የክልል መንግስቶች በየክልላቸውና በአዲስ አበባ ውስጥ ሁለት የመኖሪያ ቤቶች እንደ ክረምትና በጋ ቤት ይዘው ይገኛሉ። የህወሃት/ኢህአዲግ መንግስት የፓርላማ ተመራጮች ሌሎች የቤት ተጠቃሚዎች ናቸው። ተመራጮቹ ባለመናገራቸውና ቀኝ እጃቸውን ለድምፅ ቆጠራ ለአመታት በማውጣታቸው፤ በክረምቱ ወራት ፓርላማ ተዘግቶ ወደ ቤታቸው ሲሄዱ በሃገረ ባህል ሃኪም ‹ወጌሻ› በመታሸት ነው የተሰቀለው እጃቸው ወደታች የሚወርደው እየተባለ ይታማሉ።
በደርግ ግዜ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ለኢንባሲዎች ከ40 እስከ 50 ሽህ በብርና በዶለር ለኢንባሲዎች ይከራዩ የነበሩ ቤቶች በህወሃት የጦር አበጋዞች፣ካድሬዎችና ደህንነቶች ተወርሰው ላለፉት 23 ዓመታት በነፃ መኖሪያነት ሲያገለግሉ፤ የታጣው የህዝብ ሃብት በትንሹ ለማሳየት፤ ለምሳሌ አንድ ቤት 40,000 ሽህ ብር ለኢንባሲ ይከራይ ከነበረ 40,000 ሲባዛ 12 ወራት ይሆናል 480,000 ሽህ ብር በአመት፤ ሲሆን በሃያ ሦስት አመት ሲሰላ ደግሞ 480,000 ሲባዛ 23 ይሆናል 11,040,000 ሚሊዮን ብር ከአንድ ቤት ብቻ በነዚህ የቀን ጅቦች የኢትዮጵያ ህዝብ ተመዝብሮል ማለት ነው። ከአጠቃላዩ 17,549 ቤቶች ስንት ቢሊዮን ብር እንደተዘረፈ ለማየት የሒሳብ ሊቅ መሆን አይጠይቅም:: ትላንት በቁምጣና ሽበጥ ጫማ አዲስ አበባ የገባው የህወሃት/ኢህአዲግ የጦር አበጋዞች፣ካድሬዎችና ደህንነቶች በአዲስ አበባ ከተማ 500 ሜ/ካ ቦታ ተሰጥቶቸው ፎቅ ሰርተው ያከራያሉ፣ዛሬም በተሰጣቸው ቤት ኪራይ ይኖራሉ። እነዚሁ ሹማምንቶች ከየመጡበት ክልል ተጨማሪ 500 ሜ/ካ ቦታ የአርበኝነት ሣይሆን የባንዳነት ሥጦታ ተደርጎላቸዋል። አበው ሲተርቱ ‹ድህነት ይለመዳል፤ሃብታምነት አይለመድም› የሚሉት ብሂል ለዚህ ነው። የደርግን ስርዓት ለመጣል ስንት ታጋዬች ወድቀዋል፤ አንዴ ለአፍታ ቀና ብለው የዛሬዎቹን ሃብታም ጅቦች፤ የትላንቱን የድሃ ልጆች ቢዩችሁ ምን ይሉ!!!

በቤቶቹ ቅርምት የደደቢት ህወሃት የጦር አበጋዞችና የፖለቲካ ካድሬዎች የአንበሳውን ድርሻ ሲደርሳቸው ቀጥሎ የብአዴን፣ የኦህዴድ፣ደህዴድ ወዘተ ከቤቶቹ ቅርምት ኩርማን፣ሲሶና አስራት ቅርጫ ደርሶቸዋል። የህወሃት የጦር አበጋዞች አደዋ አደባባይ ሲግናልና ከተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ከፍ ብሎ ለ‹ኢትዮጵያ› መከላከያ ሰራዊት መኮንኖች መኖሪያነት ስም የተገነባውን ከ50 እስከ 100 የሚደርስ ምርጥ ኮንዶሚኒየም ቤቶች ለህወሃት የጦር አበጋዞች መኖሪያነት ተሰጥቶል። ከዚህም በተጨማሪ በአዲስ አበባ ከተማና በአጎራባች የኦሮሚያ ክልሎች የህወሃት የጦር

አበጋዞች፤‹የህዝብ ደህንነት›ና የፖለቲካ ካድሬዎች ከአንድም ሁለት ሦስት መሬት እየተመሩና እየሸጡ የኢትዬጵያ ህዝብን ንብረት ለአለፉት 23 ዓመታት ዘርፈዋል፡፡

በወርሃ ሚያዝያ 2006፤ በዚህ ድርጊታቸው የተበሳጩ የአዳማ፣አምቦ፣ሃሮማያና፣ መዳወላቡ ባሉ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ተቃውሞ በማሰማታቸው 45 በላይ ሰዋች ህይወታቸውን ማጣታቸውንና ብዙ ሰዋች መቁሰላቸውን የዓለም ዓቀፍ ዜና ሆኖ ሰንብቶል፡፡ ይህ የተዘረፈ የኢትዬጵያ ደሃ ህዝብ ንብረት አንድ ቀን እንደሚመለስ ጆሮ ያለው አዋጁን ይስማ!!! የህወሃት የጦር አበጋዞችና ካድሬዎች የመሬት ቅርምትና የቤቶች ነጠቃ ለአንዴም ለሁሌም ያከትማል የሚቀጥለውም መንግስት በዚህ ዓይነት የሙስና ስርዓት የመንግስት ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ (የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ) በአዋጅ ይሽራል፡፡ ቤቶቹም ከመንግስት ወደግሉ ዘርፍ ሃብትነት ይተላለፋሉ፡፡ የመንግስት ሹማምንት ቤት፣መሬትና መኪና የመሳሰሉትን ዓይነት ጥቅማ ጥቅሞችን አያገኙም፡፡ ህዝቡንም በቅንነትና በታማኝነት ያገለግላሉ፡፡
የሳዑዲ ዓረቢያ ቢሊዬነር ሼክ መሃመድ አላ-አሙዲ በሜድሮክ ስም ከመንግስት ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ (የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ) ብዙ ቤቶችን በድርጅታቸው ስም በመቆጣጠር በተለይ ሲኤምሲ (ደርግ ለኢንባሲዎች መኖሪያነት ያሠራቸው ሕንፃዎች በዶለር የሚከፈልበትን 90 ከመቶውን በመቆጣጠር) ትልቁን ቅርጫ በመውሰድ ለቤት ኪራይ በወር አስር ሚሊዬን ብር እንደተከራዩ ቢታወቅም ብዙ ግዜ የቤት ኪራይ እንደማይከፍሉ በኤጀንሲው ሠራተኞች ያታወቃል፡፡

የህወሃት/ኢህአዲግ መንግስትና የሼክ መሃመድ አላ-አሙዲ (ሜድሮክ) የሲሦ መንግስትነት ሺርክና በመንግስት ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ (የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ) ሹማምንት እስከ አጥንታቸው መቅኒ በሙሰኝነት በነቀዙ ባለስልጣናት የኢትዬጵያ ህዝብን ንብረት ተመዝብሮል፡፡ ይህንን የንቅዘት ግንኙነት ለማጋለጥ የሞከሩ ጋዜጠኞች ሁሉ ማስጠንቀቂያና ድብደባ ደርሶባቸዋል፡፡ ቀጥለን የሲዊዲሽ ዓለምዓቀፍ እድገትና ትብብር ኤጀንሲ በ2004 እኤአ ያቀረበውን 42 ገፅ ጥናት በቁንፅል በማቅረብ ፁሁፍን እናጠናቅቃለን፡፡ /sida@sida.se, www.sida.se /ድረ ገፅ ይመልከቱ፡፡

Country Economic Report 2004:4, NOVEMBER 2004 • GÖTE HANSSON
Ethiopia: Economic Performance and the Role of the Private Sector
6 - Ownership concentration
The increased role of the private sector in the Ethiopian economy outside the agriculture sector is largely due to two groups of actors, the MIDROC-group, owned by the Ethio-Saudi businessman Sheik Mohammad Hussein Al-Amoudi, and the TPLF-owned *Endowment Fund for the Rehabilitation of Tigray*, the EFFORT-group.
Sheik Al-Amoudi's business activities include agricultural, industrial and service activities. MIDROC-Ethiopia includes for example the newly completed luxury Sheraton Hotel in Addis Ababa, the Pepsi-Cola factory in Addis Ababa, the National Mining Corporation, Dashen Bank, and Nyala Insurance Company but also companies in agriculture, transport, and the construction sectors. According to informal information, MIDROC-Ethiopia also has, or has advanced, plans to go into the health and education sector, including the establishment of a private university.
It is obvious that the MIDROC-group has a size and orientation that makes it highly influential and important in the Ethiopian business life. Its activities also seem to be of a long-term character. It is of great importance that the MIDROC-group does not get a dominant position within a specific sector or market. The strategy so far seems to be to create a largely diversified business conglomerate covering most business sectors of the economy. However, from the perspective of market concentration it is essential to follow closely the development of MIDROC Ethiopia and how it uses its actual and potential market power. Even though Sheik Mohammad Hussein Al-Amoudi's MIDROC group's business activities are widespread and increasing, this group has not created a debate and a criticism that can compete with the debate about and the criticism of the other non-government business group, the EFFORTgroup.
As is clear from its name, this group has both its objective and its activities largely directed towards the Tigray region. Like the MIDROCgroup, the EFFORT-group operates in more or less all business sectors. According to information from EFFORT, this group was founded in

August 1995 and its working capital is derived from resources endowed to the Foundation. EFFORT invests in several sectors of the Ethiopian economy (EFFORT 1997). Each of the Fund's companies "is an independent commercial entity registered under the commercial code of Ethiopia" (ibid.). Furthermore, "The activities of the Endowment Fund for the rehabilitation of Tigray complement government development programs" (ibid.).27

The EFFORT-group has organised itself along the following business sector lines:

– Agriculture and agro-processing,– Construction and engineering,– Manufacturing,– Mining,

– Services, including banking (Wegagan) and transports (TESCO)

According to information obtained from interviews with private sector representatives, it seems so far to be mainly in the transport sector that the EFFORT-group has reached a dominant position. According to information from EFFORT, the Trans-Ethiopia Company's (TESCO) share of the Ethiopian freight market was 35 per cent in the fiscal year 1995/96.

It is obvious that the above-mentioned market position of TESCO, together with rules and procedures in the transport sector, easily lead to distortions and a feeling of discrimination among private individual truckers and trucking associations.

Considering the crucial role of the transport sector in Ethiopia, it is important to follow and analyse the situation in the transport market carefully and for the government to take necessary steps in the regulation and implementation of its transport policy so that efficiency is promoted and the risks of or actual abuses of distortionary market power are eliminated or reduced. The situation in the trucking industry should also be studied as an example of the problems that can arise as a result of the close links between the ruling government and party-owned private enterprises. Through such a critical study the risks of unfair competition and social losses due to inefficiency can be reduced or even eliminated.

As noted above, the EFFORT-group has its basis in the Tigray People's Liberation Front (TPLF) even though it is formally an independent share company. From the point of view of efficient competition, as indicated by the experience from the transport sector and revealed in the surveys about the business climate mentioned above, the close relation between TPLF and the present Ethiopian government easily creates doubts about the equal treatment of EFFORT-companies and other non-party-related private companies. As there is no efficient and working commercial legislation, these doubts, well founded or not, easily create problems concerning the government's legitimacy and the credibility of its private sector policies.

The doubts about the equal treatment of various non-government private actors within a sector, independently of the form of ownership and organisation, will most likely increase with the growth of party related business. Therefore, it may turn out to be a severe problem that the Ethiopian government decided to allow the party to run businesses in October 1997.

There are at least two potential motives behind this change in policy. The change may be seen as a way to mobilise and utilise all available resources in the development process. However, it may also be seen as a way for the EPRDF to keep control over the more market-oriented and privatised economy, not only from the government offices but also as an active owner of business corporations.28

Turning to the likely effects of the new policy, on the one hand, this change in policy can contribute to more regionally balanced economic activities than those that now characterize rural Ethiopia where non peasant activities as a rule are in an infant stage. The exception today is Tigray, where the EFFORT-group clearly gives this region important non-agricultural resource. On the other hand, the increased involvement of the party in the business community easily creates negative effects in terms of reduced credibility and legitimacy of the government in the Ethiopian and international business community. There is an obvious risk that these negative effects will more than outweigh the shortrun positive effects of mobilising and allocating party funds to the development of non-government economic activities.

Source:-SWEDISH INTERNATIONAL DEVELOPMENT COOPERATION AGENCY, sida@sida.se, www.sida.se